17ኛ አመት ቁጥር 4

17th Year No. 4

ባህር ዳር ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም

Bahir Dar 27th Jan, 2012

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG
# OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
# IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 16.50 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |



## ማውጫ

**ደንብ ቁጥር 91/2004 ዓ.ም**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## CONTENTS

**Regulation No. 91/2012**

The Amhara National Regional State Public Procurement and Property Disposal Service Establishment, Council of the Regional Government Regulation

## ደንብ ቁጥር 91/2004 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## Regulation No. 91/2012

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED FOR THE ESTABLISHMENT OF PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY DISPOSAL SERVICE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

የመንግስት ግዥ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በተበታተነ መንገድ በመፈፀሙ ምክንያት የሚባክነዉን ጊዜና ወጪ መቆጠብ እና የግዥ አገልግሎት ስራን በጥቂት የሰዉ ኃይል በመሥራት ዉጤታማ የሰዉ ኃይል አጠቃቀም እንዲኖር ማስቻል በመታመኑ፤

WHEREAS, it is believed that enabling the existence of effective utilization of man power through saving the wastage of time and expense and performing the activity of procurement service with a small amount of man power due to public procurement which has so far been exercised by various offices in a dispersed manner;

አገልግሎቱ የግዥ ህጉንና ሂደቱን ጠንቅቀዉ በሚያዉቁ ባለሙያዎች ግዥ እንዲፈፀም ዕድል ስለሚሰጥ፣ ግዥ በዕቅድ እንዲመራ ስለሚረዳና ግልጽ ጨረታን በማበረታታት የተሻለ ብቃትና አቅም ያላቸዉን አቅራቢዎች ስለሚጋብዝ፤ እንዲሁም የግዥ አፈፃፀም መረጃን በአንድ ቦታ በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል በመሆኑ እና በወል የሚፈለጉ ዕቃና አገልግሎቶች ስታንዳርድ እንዲኖር በማድረግ ለመስሪያ ቤቶች የሚገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች አንድ ወጥና ተመሳሳይ እንዲሆኑ ስለሚያስችል፤

WHEREAS, the service enables to render the opportunity for the procurement to be executed by professionals who are adequately knowledgeable with the law and the process of purchasing, helps the procurement to be managed by plan, invites suppliers with better efficiency and capacity through encouraging open tender, facilities the easy availability of information as to the execution of procurement in one place and causes the goods and services to be purchased for offices to be similar and consistent by realizing the existence of standard for commonly demanded goods and services;

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ንብረቶች ሊወገዱ የሚገባበትን መንገድ ስርአት ባለዉ መልኩ በመምራት ይባክን የነበረዉን ሀብት በማዳን የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is necessary to protect the interest of the Government by taking care of the public bodies property that would otherwise have been in loss through managing the process of its disposal in a systematic way;

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ(7) እና በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 ዓ.ም አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ(1) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህን ደንብ አዉጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, pursuant to the powers vested in it under the provisions of Art.58 Sub-Art./7/ of the Revised Regional Constitution and Art. 47 Sub-Art./1/ of the Public Procurement and Property Administration Proclamation No 179/2011, hereby issues this regulation as follows.

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠዉ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-
   ሀ. **"አዋጅ"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 ዓ.ም ነዉ፡፡
   ለ. **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ነዉ፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ ሁለት ስር የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. መቋቋም

1. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት (ከዚህ በኋላ "አገልግሎቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰዉነት ያለዉ የክልሉ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የአገልግሎቱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፡፡

# PART ONE
# GENERAL

## 1. Short Title

This regulation may be cited as the "Amhara National Regional State Public Procurement and Property Disposal Service Establishment, Council of the Regional Government Regulation No. ***91/2012***".

## 2. Definitions

1. Unless the context requires otherwise, in this regulation:
   a) **"Proclamation "** shall mean the Amhara National Regional State Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 179/2011;
   b) **"Bureau"** shall mean the Amhara National Regional State Finance and Economic Development Bureau;
2. The definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

## 3. Establishment

1. There is hereby established, the Public Procurement and Property Disposal Service, hereinafter referred to as the "Service" as the Regional government office, having its own autonomy and legal personality, as per this regulation;
2. The service shall be accountable to the Bureau;

## 4. ዓላማዎች

አገልግሎቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጃዊ ጠቀሜታ ያላቸዉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘዉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ፣ በተገቢዉ ጊዜና በተፈላጊዉ ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፣
2. ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ከሚወሰነዉ የእቃዎች የመነሻ ዋጋ ግምት በላይ የሆኑና በሽያጭ እንዲወገዱ ዉሣኔ የተሰጠባቸዉ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀናጀና በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻል፣
3. ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በዕቃና አገልግሎት ግዥ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ፤

## 5. ዋና መስሪያ ቤት

የአገልግሎቱ ዋና መሥሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል።

## 4. Objectives

The service shall have the following objectives:

1. To enable the timely provision of goods and services which are commonly used by public bodies as well as those goods and services of similar nature and having national strategic significance in the desired quality and at fair prices attributable to the economies of scale resulting from block purchase;
2. To enable the disposal of properties belonging to public bodies, whose price is more than the estimated initial price of the goods to be decided pursuant to the directive of the bureau and the disposal of which decided upon through sale, in an integrated and expeditious manner against reasonable price;
3. To assist public developmental enterprises with regard to the procurement of goods and services as well as the disposal of property.

## 5. Head Office

The service shall have its head office in the city of Bahir Dar; provided, however, that it may establish branch offices in other places, as may be necessary.

# ክፍል ሁለት
# ስለአገልግሎቱ አቋም፣ ስልጣንና ተግባራት

## 6. አቋም

አገልግሎቱ፡-

1. የስራ አመራር ቦርድ፤
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር የሚሾም አንድ ሥራ አስኪያጅና አንድ ምክትል ስራ አስኪያጅ፤
3. ሌሎች በየደረጃዉ ለስራዉ የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 7. የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር

1. አገልግሎቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ) ዝርዝራቸዉ በቢሮዉ መመሪያ የሚወሰን የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጃዊ ጠቀሜታ ያላቸዉን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናዉናል፤

   ለ) ግምታቸዉ በቢሮዉ መመሪያ ከሚወሰነዉ የገንዘብ መጠን በላይ የሆነና በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት ሥር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ዉሣኔ የተሰጠባቸዉን ንብረቶች ይሸጣል፤

   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ቁጥሮች (ሀ) ና (ለ) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለማንኛዉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ለግሉ ዘርፍ፡

# PART TWO
# STATUS, POWERS AND DUTIES OF THE SERVICE

## 6. Status

The service shall have:

1. A Board of Management;
2. A director general and deputy director general to be appointed by the head of the regional government;
3. Other heads and employees necessary for the tasks at various levels.

## 7. Powers and Duties of the Service

1. The service shall have the following powers and duties:

   a) Carryout the procurement of goods and services falling within the list of common user items for those public bodies as well as goods and services having national strategic significance, as may be determined by the directive of the Bureau;

   b) Conduct the sale of public properties, the monetary values of which exceed the amount specified by directive of the bureau, due to be disposed pursuant to the decision of the public bodies in possession of such properties;

   c) Without prejudice to the provision of letter numbers (a) and (b) of this Sub Article hereof, it shall render:

1) በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ዉስጥና የዓለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣
2) የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

1) Domestic and international procurement service based on current market information;
2) Consultancy and training services regarding the execution of procurement;

to every public bodies as well as, up on request, to public developmental enterprises and the private sector.

2. አገልግሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ፊደል ተራ ቁጥሮች (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሮችን በሥራ ላይ ሲያዉል፡-
   ሀ) የመንግስት ግዥውና ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
   ለ) የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ዉስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲያዉቁት ያደርጋል፡፡
   ሐ) የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸዉን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ግዥ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂዊ ጠቀሜታ ያላቸዉን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ አካላቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

2. In carrying out the public procurement and disposal of public property pursuant to letter numbers /a/ and /b/ of Sub Art. /1/ of this article hereof, the service shall:
   a) Ensure that the duty of public procurement and property disposal is executed in accordance with the Proclamation, regulations and directives issued for the implementation of the Proclamation;
   b) Complete the procurement procedures for domestic procurement of goods and services which are common user items to public bodies, enter into a frame work contract and notify same to the public bodies;
   c) Carryout international procurement of goods and services which are common user items to public bodies and procurement of goods and services which have national strategic significance and effect delivery of such goods and services to the user entities;

መ) ልዩ ሙያዊ እዉቀት በሚያስፈልጋቸዉ ጉዳዮች ረገድ ይህንኑ አግባብ ካላቸዉ መንግስታዊ ተቋማት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

d) Request for professional support from appropriate governmental institutions on matters that require special expertise.

## 8. ስለቦርዱ አባላት

1. ቦርዱ ሰብሳቢዉን ጨምሮ ከ5-7 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል፤
2. የአገልግሎቱ ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ አስረጅ በመሆን ይሰራል፤
3. ቦርዱ የራሱን ፀሐፊ ይሰይማል፤
4. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በቢሮዉ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰየሙ ይሆናሉ፡፡
5. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት ተጠሪነታቸዉ ለቢሮዉ ይሆናል፡፡
6. የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሶስት አመት ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ለተጨማሪ ሶስት ዓመት ሊራዘም ይችላል፡፡

## 8. Membership of the Board

1. The board shall, including the chairperson, have members ranging from 5 through 7.
2. The manager of the Service shall act in the capacity of an expert for the board.
3. The board shall designate its own secretary.
4. The chairperson and members of the board shall be designated by the head of the regional government upon their nomination by the Bureau.
5. The accountability of the chairperson and members of the board shall be to the Bureau.
6. The tenure of the board members shall be three years; provided, however, that it may be extended for an additional term of three years, as deemed necessary.

## 9. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አገልግሎቱን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል
2. የአገልግሎቱን ረቂቅ ስትራቴጅዎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፤
3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ/1/(ሀ) መሰረት የሚፈጸሙ ከፍተኛ ግዥዎችን መርምሮ ያጸድቃል፤
4. የአገልግሎቱን ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለቢሮዉ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

## 9. Powers and Duties of the Board

The board shall have the following powers and duties:

1. Direct over and supervise the Service;
2. Examine and approve the draft strategies and operational directives of the Service; and follow-up the implementation of same;
3. Review and approve the higher procurements performed pursuant to Art. 6 Sub-Art./1/ (a) of this Regulation;
4. Review and submit the annual work program and budget of the Service to the bureau as well as ensure the implementation of same upon approval thereof;

5. የአገልግሎቱን ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ያፀድቃል፤ የዉጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ይሰማል፤ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት አስፈላጊዉ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤
6. አገልግሎቱ የሚያስከፍለዉን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፤
7. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

## 10. ስለቦርዱ ስብሰባና የዉሳኔ አሰጣጥ ስነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢዉ ጥሪ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የቦርዱ ዉሣኔ የሚተላለፈዉ በስብሰባዉ ከተገኙ አባላት በአብዛኛዉ ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፁ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 11. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

1. የቦርዱ አጠቃላይ አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ ስራ አስኪያጁ የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የአገልግሎቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

5. Approve the annual financial report of the Service, hear the report of external auditors and ensure that the appropriate corrective measure is taken on the basis of such reports;
6. Submit to and have the amount of service charge of the Service decided by the Council of the Regional Government as well as ensure its implementation thereof;
7. Form advisory committees, as deemed necessary.

## 10. Meeting and Decision Making Procedure of the Board

1. The Board shall convene its meeting once in there months. It may, however, hold a meeting at the call of the chairperson, as deemed necessary.
2. There shall be a quorum where more than half of its members are present at a meeting of the Board.
3. The decision of the Board shall pass where it is supported by the majority members present at the meeting. In case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.
4. Without prejudice to the provisions of this Article hereof, the Board may issue its own meeting procedural directive thereof.

## 11. Powers and Duties of the Manager

1. The Manager shall, being the chief executive officer, subject to the overall guidance of the Board, direct and administer the activities of the Service.

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ /6/ ስር የተመለ ከቱትን የአገልግሎቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፤

ለ) የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግስት በሚጸድቅ መመሪያ መሰረት የአገልግሎቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ)የአገልግሎቱን ረቂቅ ስትራቴጃዊ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፣ በመንግስት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያዉላል፤

መ)ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች ሁሉ አገልግሎቱን ይወክላል፤

ሠ) ስለ አገልግሎቱ የስራ እንቅስቃሴ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

ረ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

3. ስራ አስኪያጁ ለአገልግሎቱ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለአገልግሎቱ ምክትል ስራ አስኪያጅና ለሌሎች ሠራተኞች በዉክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2. Without prejudice to the generality stipulated under Sub Art./1/ of this Article hereof; the manager shall:
   a) Exercise the powers and duties of the Service provided for under Art. /6/ of this Regulation;
   b) Hire and administer the employees of the Service in accordance with a directive to be approved by the Government following the basic principles of the Regional Civil Service laws;
   c) Prepare and submit the draft strategic plan, annual work program and budget of the Service to the Board and implement same upon its approval by the Government;
   d) Represent the Service in all its dealings to be carried out with third parties;
   e) Submit periodic reports to the Board on the activities of the Service;
   f) Carryout such other related activities as are referred to him by the Board.
3. The Manager may delegate part of his powers and duties to the Deputy Manager and other employees of the Service to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Service.

# ክፍል ሦስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 12. የአገልግሎቱ የበጀት ምንጭ

የአገልግሎቱ በጀት ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል፡

1. በመንግስት የሚመደብ በጀት
2. ከሌሎች ምንጮች

## 13. ስለሂሳብ መዛግብት አያያዝና ምርመራ

1. አገልግሎቱ ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትንና የሂሳብ ሰነዶችን ይይዛል፡፡
2. የአገልግሎቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸዉ ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡.

## 14. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸዉም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፤

## 15. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር
ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም.
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

# PART THREE
# MISCELANEOUS PROVISIONS

## 12. Budgetary Source of the Service

The budget of the Service shall be generated from the following:

1. Budget to be allocated by the government.
2. Other sources.

## 13. Maintenance of Books of Account and Auditing

1. The Service shall maintain accurate books and documents of account.
2. The books of account and financial related documents of the Service shall be audited annually by the Office of the Auditor General of the Regional State or those auditors designated by same.

## 14. Inapplicable Laws

No other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall be applicable with respect to matters covered for therein.

## 15. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the date of its publication on the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This **27th** day of January,***2012***
Ayalew Gobezie
Head of Government
of the Amhara National Regional State